**በኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት**
**የፓርክ እና የመዝናኛ መምሪያ**
**የትብብር እና የልማት ክፍል**

# DPR የበጎ ፈቃድ ሠራተኛዎች

የዲሲ የፓርኮችና መዝናኛ መምሪያ (DPR) በርካታ ጨዋታ እና አስደሳች የበጎ ፈቃድ የሥራ እድል ይሰጣል። ተልዕኮአችን የተቀናጁ ፕሮግራሞች፣ እንቅስቃሴዎች እና ዝግጅቶች፣ እንዲሁም ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ውብ ክፍት ቦታዎች እና የመዝናኛ አገልግሎቶች በገቢ መጠን እና ጥራት ያላቸው አገልግሎቶችን በእኩልነት በማቅረብ የዲሲ ነዋሪዎችን እና ጎብኚዎችን ደህንነት ማሳደግ ነው።

የDPR ጠንካራ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች መነሻ በርካታ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች ዕድሎችን፣ የሚከተክሉትን ጨምሮ፣ የሚያካትት የተልዕኮው ክፍል ነው፣

- የመዝናኛ ማዕከል ሠራተኞችን ማገዝ
- ማሠልጠን እና ማማከር
- የDPR ፓርኮችን፣ የአትክልት ቦታዎኦችን እና የተፈጥሮ ስፍራዎችን ማሳመር
- የማህበረሰብ የፅዳት ጥረቶችን ማዘጋጀት
- በDPR ቁልፍ የሆኑ ዝግጅቶች የእገዛ አገልግሎት መስጠት

**የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ማን ነው?**

የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ያለ ክፍያ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ሳይጠብቅ ለDPR አገልግሎት ለመስጠት ምርጫ ያደረገ ሰው ነው። የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች፤ ወጣት፣ አዛውንት፣ የአካል ጉዳተኛ፣ ሥራ ያለው ወይም ሥራ የሌለው፣ የማንኛውም ዜግነት ወይም የዘር ሁኔታ ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ማንኛውንም የበጎ ፈቃድ እንቅስቃሴ ከማድረጉ በፊት የDPR የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ማረጋገጫ ሂደትን ያጠናቀቀና በህጋዊ መንገድ የተፈቀደለት መሆን አለበት።

**የበጎ ፈቃደኞች ዓይነት**

<u>የትምህርት ቤት/የአጭር ጊዜ/የኮሌጅ በጎ ፈቃድ ሠራኞች</u>
ከ17 ዓመት በታች የሆኑ ወጣት በጎ ፈቃደ ሠራተኞች የወላጆቻቸው የስምምነት ፍቃድ ያስፈልጋቸዋል። 17 ዓመት እና በታች ለሆኑ የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች የማንነት ማጣሪያ አያስፈልጋቸውም። ተማሪዎች አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት የትምህርት ቤት መረጃዎቻቸውን ለDPR ሠራተኛ ማቅረብ አለባቸው። የDPR ሠራተኛ የተማሪዎችን የሰዓት መመዝገቢያ እና የተፈረሙ መረጃዎች ቅጂ ማስቀመጥ ይኖርበታል። 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው የበጎ ፈቃድ ሠራተኞች፣ የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ማረጋገጫ ሂደቱን ማጠናቀቅ አለባቸው።

<u>የማህበረሰብ አገልግሎት በጎ ፍቃድ ሠራተኞች/የማሳመር ፕሮጀክቶች (የአንድ ጊዜ አገልግሎት)</u>
DPR የማህበረሰብ ማሻሻያዎችን እንደ ጽዳት እና የማሳመር ፕሮጀክቶችን የመሳሠሉ የአንድ ጊዜ ዝግጅት እንዲያካሄዱ ለግለሰቦች፣ ለድርጅቶች፣ እና የሲቪክ ቡድኖች አገልግሎት ይሰጣል። የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች የማህበረሰቡን ሁሉንም ዜጋዎች የማጠቃለል ኃላፊነትን ለማጠናከር ማህበረሰብን የመርዳት ስሜትን ይገፋፋል። የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት መሪው የDPRን የማህበረሰብ ዓላማ ቅጽ መሙላት አለበት። ይህ ቅጽ ለማጽደቅ ወደ አካባቢው ሥራ አስኪያጅ ይላካል።

<u>አስፈላጊ የማህበረሰብ ተከላካይ አገልግሎት    Mandatory Defender Community Service</u>
DPR በአሁኑ ጊዜ የማህበረሰብ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰዓቶች የሚፈልጉ በፍርድ ቤት በተቀጠሩ ተከራካሪዎችን አይቀበልም።    የDPR ሠራተኞች ከማንኛውም የDC፣ MD እና VA የጠበቃ ቢሮ ወይም የፍርድ ቤት ቢሮዎች የሚመጡ ሰነዶችን ማጽደቅ ወይም መፈረም የለባቸውም።

ስለ በጎ ፈቃድ ሠራተኛ ፕሮግራም ወይም የማህበረሰብ አገልግሎት የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ወይም ጥያቄ ካለዎት እባክዎን የሚከተለውን ያነጋግሩ፡

አሊስ ሚለር
የበጎ ፈቃድ ሠራተኛ ፕሮግራም፣ ሥራ አስኪያጅ
dpr.volunteer@dc.gov
**202-671-0129**